
‹‹ምን ሁናችኋል?!
መገጭ እንዴት ብሎ በክረምት
ሊጠራ ይችላል?!››



# አልማ እና የአውራ አምባ ማህበረሰብ

ዛሬ ዛሬ የእህል ወፍጮ መካከለኛ ገቢ ያላቸው የከተማና የገጠር ነዋሪዎች ሁሉ በቀላሉ እየገዙ ለየአካባቢያቸው አገልግሎት የሚያውሉት የንግድ ዘርፍ ነው። ቀደም ሲል ግን በጥቂት ከተሞች ካልሆነ በቀር በተለይም በገጠሩ ክፍል ያልተስፋፋ ነበር።

ይህንን ችግር በመረዳት አማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) በአማራ ብሔራዊ ክልል የተለያዩ የገጠር ክፍሎች ከ38 በላይ የእህል ወፍጮዎችን መትከሉን እናስታውሳለን። እነዚህ ወፍጮዎች የገጠር ነዋሪዎችን ሥራ ፈትተው ራቅ ወዳሉ ከተሞች ወፍጮ ፍለጋ ከመሄድ የታደጓቸው፣ ሴቶችን ከድንጋይ ወፍጮ ከሚያታግልና መጅ ከሚያስገፋ የሥራ ጫና የገላገሏቸው መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም። ይህን መሰል ማህበራዊ ችግር ከማቃለል በተጨማሪም፣ በአልማ ወፍጮ ለተለገሳቸው ማህበረሰቦች ሁሉ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም ነበራቸው። የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት ግን



እሷም ሆነች እሱ ጠምደው ያርሳሉ፡፡
እሱም ሆነ እሷ ቀጭን ይፈትላሉ፡፡

ከአልማ የተሰጣቸውን የእህል ወፍጮ ጠቀሜታ የሚለኩት ከዚህ እጅግ በላቀ ሚዛን ነው፡፡

ለዚህ መፅሔት ዝግጅት መረጃ እናጠናቅር ዘንድ ወደ አውራ አምባ ቀበሌ ጎራ ብለን ነበር፡፡ በልዩ የአኗኗር ዘይቤአቸው የሚታወቁት የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት የሚኖሩባት ልዩ ጎጥም ‹‹ጡረኝ›› ወይም ‹‹ታይካ›› መሰኘቷን በእንግድነት ከተቀበለችን ወይዘሮ ከተረዳን በኋላ የተሳካ ጉብኝት ልናደርግ ችለናል፡፡

ወይዘሮ እናነይ ክብረት የማህበረሰቡ እንግዳተቀባይናአስጎብኝመሆኗንም ነግራናለች፡፡ ከወይዘሮ እናነይ ጋር ቃለ ልውውጥ እያደረግን እያለን ‹‹ከአልማ የተሰጣቻችሁ ወፍጮ ዛሬም ድረስ ትኖር ይሆን? ›› የሚል ጥያቄ አነሳን፡፡ መልሷም ‹‹ባትኖርም ትኖራለች›› የሚል ነበር፡፡ ውሉን ያልለየ፣ ‹‹አለች›› ወይም ‹‹የለችም›› የሚል ቁርጠኛ ቃል ያልሰጠ፣ ባለ መንታ መንገድ መልስ መስሎ ታየን፡፡ ፈረንጆቹ Paradoxical የሚሉትን ዓይነትና እርስ በርሳቸው በሚቃረኑ ሃሳቦች የተዋቀረ፣ ነገር ግን የተጋጩ የሚመስሉትንሃሳቦችየሚያስታርቅ ምክንያታዊ ትንታኔ የሚሻ መልስ እንደሚሆን በመገመታችን ችላ ብለን አልዘለልነውም፡፡ እንዲያውም የጉጉት ስሜት ጭሮብን ቀልባችንን ሰጥተን ልናስተባቃው ችለናል፡፡ እንዲብራራልንም ጠየቅን፡፡

ወይዘሮ እናነይ ክብረት ማህበረሰባቸው ያለፈበትን የኋላ ታሪክ መነሻ ካላደረገች ይህን ጉዳይ አግባብ ባለው ሁኔታ ማስረዳት እንደሚያዳግት አሳሰበችንና የሆነውን ሁሉ ተረከችልን፡፡ ከሰባት ዓመት በፊት አልማ በተከለላቸው የእህል ወፍጮ የተነሳን ጥያቄና 21 ዓመት ወደ ኋላ ተንደርድሮ የሚጀምር መልስን ምን ግጥም ያገጣጥማቸዋል? ለማንኛውም ወይዘሮ እናነይ ክብረት ወደሰጡን መልስ እንሸጋገር፡፡

‹‹የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት አሁን ከምንገኝበት መንደር ተፈናቅለን በ1980 ዓ.ም ወደ ደቡብ የአገራችን ክፍል ወደ ቦንጋ ተሰደን ነበር፡፡ ለስደቱ መነሻው ‹የዚህን አካባቢ ሕብረተሰብ ባሕል አትቀበሉም› መባላችን ነው፡፡ በእርግጥ አውራ አምባዎችን ከሌላው የሚለዩን አስተሳሰቦችና ድርጊቶች አሉን፡፡ ዋናዎቹ አራት ናቸው፡፡

‹‹በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሴቶችና ወንዶች እኩል እንደሆኑ



*ወ/ሮ እናነይ ክብረት*
*የአውራ አምባ ማህበረሰብ እንግዳ ተቀባይና አስጎብኝ*

እናምናለን፡፡ ፈጣሪ ሰውን አልከፈለም፡፡ ሴቶች ከወንዶች የሚለዩት በማርገዛቸው፣ በመውለዳቸውና በማጥባታቸው ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ  ልዩነት እንጂ እኩል አለመሆን አይደለም፡፡ ስለዚህም፣ የወንድና የሴት ተብሎ የተከፈለ ሥራ የለንም፡፡ ሁላችንም የቤት ውስጡንም ሆነ የውጪውን ሥራ እንሰራለን፡፡

‹‹ይህን ሲቃወሙን ‹ሴት እኩል ከሆነች ማን አዛዥ፣ ማን ታዛዥ ሊሆን ነው? ወንድ ወደ ማጀት ገብቶ ሊያበስል ነው ወይ? ከሚስቱ  ተጣልቶ ሸሽታ ወደ ማጀት ብትገባ እንኳን አይከተላትም፡፡ ቢርበው ከማጀት ገብቶ ሞሰብ ከፍቶ አይበላም› ይሉናል፡፡

‹‹ሁለተኛው፣ የሕፃናት መብት መከበር እንዳለበት እናምናለን፡፡ በዚህም፣ ‹ልጅ የሰጡትን ይብላ፣ ያዘዙትን ይሥራ እንጂ የምን የልጅ እኩልነት ነው›  በሚል ይቃወሙናል፡፡

‹‹አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞችን የመደገፍ ኃላፊነት እንዳለብን ስለምናምንም በተግባር እንፈፅመዋለን፡፡ ሌሎች ግን ‹ማን የማንን አረጋውያንና አካል ጉዳተኛ ይጦራል? ከተወሰነ የዘር ትውልድ በኋላ ዘመድ አይደለም፣ ምናችንም አይደለም› ይላሉ፡፡ በአውራ አምባ እምነት ግን ዘር በዛ እንጂ ግንዱ አልተለወጠም፡፡

‹‹አለመስረቅ፣ አለመዋሸት፣  አለመጉዳት፣ በራሳችን እንዲሆን የማንፈልገውን   በሌሎች ላይ አለመፈፀም የመሳሰሉት የምንከተላቸው የሥነ-ምግባር መመሪያዎቻችን ናቸው፡፡ ይህን የሚቃወሙንም ‹ውሸት የገበያ መሸጫችን ነው፡፡ እየራበኝ እናንተ ልትበሉ ነው ወይ? ከራበኝ እሰርቃለሁ፡፡ ሃሜት ይጥፋ የምትሉት ቡና ስንጠጣ ምን እናውራ? ምቀኝነት እንዴት ከሰው ላይ ሊጠፋ ይችላል?› እያሉ ነው፡፡

‹‹ከዚህ በተነሳ ‹ባሕላችንን አቆሸሹ፣ አጠፉ› ተብለን ጉዳዩንም ወደ ፖለቲካ አዙረው፣ የመንግሥት ተቃዋሚ ናቸው አሉን፡፡ የደርግ መንግሥትም በእኛ ላይ ግድያ መፈፀም ጀመረ፡፡ በተለይም በማህበረሰቡ መሥራች ዙምራ ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ነው ከዚህ ጠፍተን የሄድነውና ወደ ደቡብ የተሰደድነው፡፡

‹‹ኢሕአዴግ ከገባ በኋላ ግማሾቻችን በ1985 የተቀሩት በ1986 ዓ.ም ተመልሰን መጣን፡፡ የመጀመሪያ ቦታችን ላይ ስንሰፍር ሰው መሬታችንንና ንብረታችንን ተከፋፍሎ ጠበቀን፡፡ ተመልሰንም ‹እስኪ የአሁኑ መንግሥት ያድናችሁ እንደሆነ እናያለን› እያሉ እኛን የማጥቃት ሙከራም ያደርጉ ነበር፡፡ በገበያም ምንም ነገር አይሸጡልንም፡፡ ወደ ወፍጮ ሄደንም እህል ማስፈጨት አንችልም፡፡

‹‹አልማ በ1994 ዓ.ም የእህል ወፍጮ ተከለልን፡፡ ከወፍጮ ቤትም እንዳንደርስ ተከልክለን በተገለልንበት ጊዜ ከአልማ ወፍጮ ማግኘታችን እጅግ የተለየ ስሜት የሚፈጥር ድጋፍ ነው፡፡

‹‹ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ወፍጪችን ስትጮኽ የአካባቢው ሕብረተሰብ መስማት ጀመረ፡፡ በቅርባቸው የሚገኝ ወፍጮ ስለሆነ ወደ እኛ እየመጡ ማስፈጨትን ምርጫቸው አደረጉ፡፡ እህላቸውን ሰጥተውንም ወደ የሥራቸው ይሄዳሉ፡፡ ፈጭተን እንጠብቃቸዋለን፡፡ በፍቅር ስለምናስተናግዳቸውና በአደራ የሰጡንን የሚፈጭ እህልና ሥራ ሳናጓድል በሙሉ ታማኝነት ስለምናስረክባቸው ለማስፈጨት ብለው ሥራቸውን አያስተጓጉሉም፡፡

‹‹በዚህ ዓይነት ሂደት እየተግባባንና እየተቀራረብን ሄድን፡፡ ለማስፈጨት መምጣታቸው ማንነታችንን እንዲያውቁ ረዳቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሕብረተሰቡ ለእኛ ያለው ፍቅርና አክብሮት በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡ ሴቶቹም እንደእኛ ማህበረሰብ ሴቶች ጠምደው ማረስ ጀምረዋል፡፡ ወደኛ እየመጡም ሽቀጣሽቀጥ ይገዛሉ፡፡ የበፊቱ ድርጊታቸው እየቆጫቸው ‹እኛ እድሜያችንን በከንቱ ፈጀነው፣ ለልጆቻችን መሰረቶቻቸው ናችሁ፣ እናንተን ያቆይልን› ይሉናል፡፡